የምዕራፍ ሰባት የክለሳ ጥያቄዎች ገፅ 91-92

- የእውነት ሀሰትና የአዛምድ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ፃፉና ስሩ።

ቀሪዎቹን ጥያቄዎች በመፃህፋችሁ ላይ ስሩ።

## ምዕራፍ ሰምንት

## ራስን መቻል

### ራስን የመቻል ምንነት

- ራስን መቻል ማለት የራስን ጉልበትና አቅም ጠንቀቆ በማወቅ በዚያው መጠን የሚቻለውን ነገር ሁሉ በራስ ተነሳሽነት ጠንክሮ መስራት ነው።

የራስን መቻል መገለጫዎች

- በራስ መተማመን
- ራስን መሆን
- የሌሎችን ሀሳብ ማክበር
- ችግር ፈቺ መሆን
- ለላቀ ስራ ክብር መስጠት
- ችሎታን ማወቅ

### በራስ መተማመን

- በራስ መተማመን ማለት የራስን አቅም ጠንቅቆ በማወቅ በሚሰሩት ስራ ላይ እርግጠኛ መሆን መቻል ነው።
- በራስ ለመተማመን ጠንክሮ መስራትና እውቀትን ማዳበር መሰረታዊ ነገሮች ናቸው።

### በአቋም መፅናት

- ማንኛውም ሰው አንድን ጉዳይ ለመፈፀም ቆርጦ መነሳቱን ሲገለፅ አቋም ይዟል ይባላል።

## አቋም መያዝና መፅናትን በተመለከተ፡-

- በጉዳይ ላይ በቅድሚ ጊዜ ወስዶ ማሰብ፣
- ለመያዝ የተፈለገውን አቋም ከቤተሰብና ከራስ እና ከሀገር ደህንነት እና ጥቅም ጋር ማገናዘብ
- የራስን ነፃ አቋም መያዝና ያመኑበትን ሀሳብና አመለካከት በነፃነት ማራመድ መሰረታዊ ነገሮች ናቸው።

## ለራሳችን ለሚኖረን ተሳሳተ ግንዛቤ የሚገለፅባቸው ባህሪያት

## የበላይነት ስሜት

- የበላይነት ስሜት ራስን ብቻ ከፍ አድርጎ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ከመመልከት የሚመነጭ ነው።

## የበታችነት ስሜት

- የበታችንነት ስሜት የሚመነጨው ራስን ዝቅ አድርጎ ከመመልከት ነው።

## ለሀገር እድገትና ብልፅግና መስራት

ሀገራችንን ማሳደግና ማበልፀግ የምንችለው በልማት ስራዎች ላይ ሁሉ ተጋግዘን በአንድ መንፈስ ስንሰራ ብቻ ነው።

## ለሀገር እድገትና ብልፅግና ከሚጎዱ ተግባራት

# ኮንትሮባንድ

ኮንትሮባንድ ማለት ከሁለት የጣሊያንኛ ቃላት የተመሰረተ ነው። <<ኮንትራ>> ማለት መቃወም፣መፃረር እና ተቃራኒ መሆን ማለት ሲሆን <<ባንድ ማለት አዋጅ ህግንና መመሪያን ያጠቃልላል።

የኮንትሮባንድ ንግድ ማለት ህግንና መመሪያን በመተላለፍ በመቃወም የማድረግ የንግድ እንቅስቃሴ ነው።

በአጠቃላይ ኮንትሮባንድ በአሁኑ ጊዜ ድርጊቱም፡-

- ለሽብርተኝነት የገንዘብ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፣
- የመንግስት ገቢን ያሳጣል
- ጥራትና ደረጃውን ያልጠበቀ ሸቀጦች እና ያልተፈቀዱ የጦር መሳሪያዎች ወደ ሀገር እንዲገቡ በማድረግ የሀገርን ሰላምና ኢኮኖሚ፣ የህዝብና ማህበራዊ ህይወት እና ጤናን በማቃወስ ላይ የሚገኝ ከባድ ወንጀል ነው።